# ካላይ ከእጽዋት ጋር ትነጋገራለች

Ursula Nafula
Jesse Pietersen
Mezemir Girma
Amharic
Level 2

(imageless edition)

ይቺ ካላይ ነች። ዕድሜዋ 7 ዓመት ነው። የስሟ ትርጉም በቋንቋዋ በሉቡኩሱ ‹‹ጥሩዋ ልጅ›› ማለት ነው።

ካላይ ከእንቅልፏ ስትነሣ ከአንድ የብርቱካን ዛፍ ጋር ትነጋገራለች። ‹‹እባክህ አንተ የብርቱካን ዛፍ ትልቅ ሁንና ብዙ የበሳሰሉ ብርቱካኖችን ስጠን›› ትለዋለች።

ካላይ ወደ ትምህርት ቤት ትሄዳለች።
በመንገዷም ላይ ከሳሩ ጋር ታወራለች።
‹‹እባክህ ሳር አረንጓዴነትህን ግፋበት እንጂ
እንዳትደርቅ።››

ካላይ የዱር አበቦችን አልፋ ሄደች። ‹‹እባካችሁ አበቦች ለጌጥ ጸጉሬ ላይ እንዳረጋችሁ ማበባችሁን ቀጥሉ።››

በትምህርት ቤት ግቢ ካለው ዛፍ ጋርም ካላይ ትነጋገራለች። ‹‹እባክህ አንተ ዛፍ ከጥላው ስር ቁጯ ብለን እንድናነብ ትላልቅ ቅርንጫፎችን አብቅልልን።››

ካላይ በትምህርት ቤቷ ዙሪያ ካለው ቁጥቋጦም ጋር ታወራለች። ‹‹ጠንካራ ሆናችሁ እደጉ፤ መጥፎ ሰዎች እንዳያልፉ አግዷቸው።››

ካላይ ከትምህርት ቤት ወደ ቤቷ ስትመለስ የብርቱካኑን ዛፍ አየችው። ‹‹የብርቱካን ፍሬዎችህ ገና አልበሰሉም?›› ስትል ካላይ ጠየቀችው።

‹‹የብርቱካኑ ፍሬዎች ገና አልበሰሉም›› ካላይ አለች። ‹‹ነገ እመለስና አይሃለሁ የብርቱካን ዛፍ›› አለች ካላይ። ‹‹ምናልባት ያኔ የበሰሉ የብርቱካን ፍሬዎች አዘጋጅተህ ትጠብቀኝ ይሆናል!››

# Storybooks Canada

storybookscanada.ca

## ካላይ ከእጽዋት ጋር ትነጋገራለች

Written by: Ursula Nafula
Illustrated by: Jesse Pietersen
Translated by: Mezemir Girma

This story originates from the African Storybook (africanstorybook.org) and is brought to you by Storybooks Canada in an effort to provide children's stories in Canada's many languages.

This work is licensed under a Creative Commons
Attribution 4.0 International License.